በአዲስ አበባ እ/ጉ/ከ/ም/ቤት የ2017 የመጅሊስ ምርጫ የመራጮች ምዝገባ የእረስከ አሁኑ ሂደት በተለመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ

ሰኔ 26 ቀን 2017 ሙሐረም 08 1447

አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ እ/ጉ/ከ/ም/ቤት ምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ ሰኔ 20 ቀን 2017 በአዲስ አበባ በሚገኙ 315 መስጂዶችና በመስጂድ አልባ ወረዳዎች የመራጮች ምዝገባ በመድረሳዎችና ቁርዓን ቤቶች እንደሚያስጀምር ሰኔ 19 ቀን 2017 በሠጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ያስታወቀ ሲሆን ባለፈው ሣምንት ለተከታታይ ሦስት ቀናት ማለትም አርብ፣ ቅዳሜና እሁድ የምዝገባ ሂደቱ በሁሉም ክ/ከተሞች በ320 መስጂዶችና መድረሳዎች ሲካሄድ ቆይቷል። የምዝገባ ሂደቱም ሠላማዊ የነበረ ሲሆን ይህ ታሪካዊ ጉዞ በዚህ ሁኔታ መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ነው። በየእርከኑ ያሉ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት የምርጫ ሂደቱን ሲከታተሉና አስፈላጊውን ድጋፍና ቁጥጥር ሲደርጉ የቆዩ ሲሆን ሰኔ 23 ቀን 2017 ሁሉንም ክፍለ ከተማ የምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ አመራሮች በተገኙበት ባደረግነው ስብሰባ የምዝገባ ሂደቱን አስመልክቶ ሠፋ ያለ ግምገማ ተደርጎ የሂደቱን መልካም ጎኖችና የተስተዋሉ ክፍተቶች በአግባቡ ተለይተዋል፣ ቀጣይ አቅጣጫም ተቀምጧል።

የመራጮች ምዝገባ በመስጂዶችና መስጂድ አልባ በሆኑ ወረዳዎች ደግሞ በመድረሳዎች በድምሩ በ320 ጣቢያዎች በአግባቡ መጀመሩና ሙስሊሙ ህዝብ ለመመዝገብና በምርጫው ለመሳተፍ ያለው ፍላጎትና ተነሳሽነት እንደ ጠንካራ ጎን የተወሰደ ሲሆን **የኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ስርዓት ላይ፣ የቅስቀሳ ስራ በበቂ ሁኔታ አለመሰራቱ፣ የህዝቡ በአምስቱ የምርጫ ዘርፎች መስፈርት ዙሪያ ብዥታ መፍጠር፣ ምርጫው በመስጂድ ደረጃ ለሚዋቀር የመጅሊስ እርከን የሚደረግ የተሳትፎና የውክና ምርጫ ሳይሆን ለወረዳ መጅሊስ ውክልና የሚደረግ የነዋሪነት ውክልና ነገር ግን ደግሞ መስጂዶች ለምርጫ ጣቢያነት ብቻ እንዲገለግሉ እንጂ የመስጂዱን አስተዳደራዊ መዋቅር ለመለወት የሚደረግ ምርጫ አለመሆኑን ያለመረዳት ችግር፣ የመርከዝአዳሪ ተማሪዎች የምዝገባና የውክልና አሰታጥ ጉዳይ ግልጽ ያለመሆን፣ የአንዳንድ መስጂዶች አስተዳደር ለምርጫው ሂደት የፍቃደኝነትና ትብብር ማነስና የሎጂስቲክስና ቴክኒካል የሆኑ ጉዳዮች ክፍተቶች ተስተውለዋል።**

ስለሆነም፣ ምርጫ አስፈፃሚ ቦርዱ ክፍተቶች በተስተዋሉበት በዋና ጉዳዮች ዙሪያ የሚከተሉትን ማብራሪያዎች ሰጥቷል።

1ኛ. የኤልክትሮኒክ የምዝገባ ስርዓትን በተመለከተ፣

- የኤልክትሮኒክ የምዝገባ ስርዓትን አስመልክቶ አስፈላጊው ማስተካከያና ስልጠና የተሠጠ ሲሆን በሁሉም መስጂዶች ምዝገባው በኤልክትሮኒክ የምዝገባ ስርዓት እንዲካሄድ አስፈላጊው ዝግጅት

ስለተደረገና በቂ የሠው ሀይል ስለተመደበ ተመዝጋቢዎች በሚኖሩበት ወረዳ ነዋሪነታቸውን የሚገልጽ የነዋሪነት መታወቂያ ይዘው ለምዝገባው መምጣት ይኖርባቸዋል።

2ኛ. የወረዳ ውክልናን በተመለከተ፣

- የ2017 የመጅሊስ ምርጫ ማስፈጸሚያ መመሪያው የመራጮች ምዝገባ በየመስጂዱ እንዲሆን ያደረገው **ምርጫችን በመስጂዳችን** የሚለውን የሙስሊሙን የትግል ጥያቄ መሠረት በማድረግና መስጂዶች የሙስሊሙ ዋናው መሰብሰቢያ መሆኑን፣ ሙስሊሙ በመኖሪያ ቁዬው የሚሰበሰብበት የኢባዳ ቦታና በሠላት ሠዓት በቀላሉ በብዛት የሚገኝበት በአላህና በሙስሊሙ ዘንድ የተከበረ ቦታ መሆኑን መሠረት ያደረገ እንጂ በመስጂድ ደረጃ መጅሊስ ለማዋቀርና የመስጂዶችን አስተዳደር ኮሚቴ ለመቀየር የሚደረግ የምርጫ ሂደት አለመሆኑን ይልቁኑ የዘንድሮ ምርጫ ለወረዳ መጅሊስ መዋቅር የወረዳ ም/ቤት ለማዋቀርና አልፎ የወረዳ መጅሊስ የስራ አስፈጻሚዎች፣ የስራ አመራሮችና የኦዲትና ኢንስፔክሽን ለመምረጥ በተመሳሳይ መልኩ በክፍለ ከተማ፣ በክተማ አስተዳደርና በፌደራል ደረጃ የሚደረግ ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጫ ሂደት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም፣ እያንዳንዱ ሙስሊም በቀኑ የስራ ወቅት ለሠላት የሚያዘወትርባቸው መስጂዶች ላይ ሳይሆን መኖሪያ ቤቱ በሚገኝበት ወረዳ ውስጥ በመኖሪያው አቅራቢያ ባለው መስጂድ ተመዝግቦ ለሚኖርበት ወረዳ የሚደርገው የምርጫ ተሳትፎና የወረዳውን መጅሊስ ለሚመሩ አመራሮች የሚሰጠው ውክልና መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።
- አንድ ሠው መታወቂያው የሌላ ወረዳ ሆኖ ነዋሪነቱ ግን የነዋሪነት መታወቂያ ካገኘበት ወረዳ ውጭ ከሆነና ቢያንስ ሁለት ወር በዛ ወረዳ መኖሩ ከሚሰግድበት መስጂድ ኢማም፣ የመስጂድ አስተዳደር ኮሚቴ አልያም በመስጂዱ ጀመኣ ከተረጋገጠለት ነዋሪነቱ በተረጋገጠበት ወረዳ የመምረጥ መብት አለው። በመሆኑም፣ ለሚኖርበት ወረዳ ውክልና ለመስጠት የሚደረግ የምርጫ ሂደት እንጂ የመራጮች ምዝገባ በየመስጂዱ ስለተደረገ በመስጂድ ደረጃ ለሚዋቀር የመጅሊስ እርከን የሚደረግ የተሳትፎና የውክልና ምርጫ አለመሆኑን ሊሰመርበት ይገባል።

3ኛ. የምርጫ ቅስቀሳን በተመለከተ፣

- የምርጫ ቅስቀሳን አስመልክቶ ሠፋ ያለ ስራ መሠራት እንዳለበት የተገመገመ ሲሆን በተለይ በመስጂድ ደረጃ በየሠላት ወቅትና በጁምኣ ኹጥባ ለህዝቡ መልዕክቶች በተደጋጋሚ መተላለፍ ይኖርበታል፣ የመስጂድ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች በየመስጂዱ ተገኝተው መልዕክት እንዲያስተላልፉ፣ የመስጂድ አስተዳደር ኮሚቴዎች አስፈላጊውን ትብብር እንዲደርጉና ኢማሞች በምርጫ ዙሪያ ተደጋጋሚ መልዕክቶችን እንዲስተላልፉልን ጥሪ እናደርጋለን። ከዚህ በተጨማሪ ሚዲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዙሪያ ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ስለሚችሉና አቅሙም ስላላቸው በዚህ ታሪካዊ ምርጫ ላይ የበኩላቸውን ተሳትፎ አድርገው የምርጫ ቅስቀሳ መልዕክት በቴሌቪዥን መስኮቶቻቸው በተደጋጋሚ ለህዛባችን እንዲስተላልፉልን

በሙስሊሙ ህዝብ ስም እንጠይቃለን፣ በእስከ አሁኑ ሂደት ድጋፍ ላደረጉልንና ለተባበሩን ሚዲዎች በህዝባችን ስም ለማመስገን እንወዳለን።

4ኛ. የምርጫ ዘርፎችን በተመለከተ፣

- የምርጫ ዘርፎችን አስመልክቶ በተለይ በዑለማዕ ዘርፍ ላይ የጎላ ብዥታ የተስተዋለ ሲሆን አንድ ሠው ከአምስቱ ዘርፍ በአንዱ ለመመዝገብ ሲመጣ ዘርፉ በግልጽ እሱን እንደሚመለከት እርግጠኛ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ የዑለሞች ዘርፍ ላይ የሚሳተፉት ሦስት አካላት ብቻ ናቸው። እነሱም፦ ዓሊሞች፣ ዱኣቶችና ኢማሞች ሲሆኑ ለዓሊሞች ድምፄን እሰጣለሁ፣ እኔ ዑለሞችን መርጣለሁ በማለት ዓሊም ወይም ዳዒ ወይም ኢማም ሳይሆን በዑለሞች ዘርፍ መመዝገብ አይችልም። በሌሎች ዘርፍ ለመመዝገብ እንደዚሁ ለዘርፉ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅበታል።

5ኛ. የመርከዝ አዳሪ ተማሪዎችን በተመለከተ፣

- የመርከዝ አዳሪ ተማሪዎችን አስመልክቶ ተማሪዎቹ ወደ መርከዝ ሲቀላቀሉ መርከዙ በሚገኝበት አካባቢ ነዋሪ ለመሆን ሳይሆን የዲን እውቅት ቀስመው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ነው። ስለሆነም፣ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ እድሜ ያለው ማንኛውም ሙስሊም በምርጫው የመሳተፍ ሙሉ መብት ያለው ሲሆን ይሁንና የምርጫ ውክልና የሚሰጠው ግን መርከዙ ለሚገኝበት ወረዳ ሳይሆን የመርከዝ ተማሪ ውክልና ነው። በመሆኑም፣ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የመርከዝ አዳሪ ተማሪዎች ልዩ ጣቢያና የመራጮች የምዝገባ ሂደት የሚመቻች ሲሆን ያሉበት ክፍለ ከተማና ወረዳ መሠረት ተደርጎ በመጅሊስ መዋቅር ውስጥ የመርከዝ አዳሪ ታማሪዎች በተለየ ሁኔታ ውክልና እንዲኖራቸው ይደረጋል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ በምርጫው እንዲሳተፉና በመጅሊስ መዋቅር ውስጥ ውክልና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

6ኛ. የሎጂስቲክስና ቴክኒካል ድጋፍ በተመለከተ፣

- ማንኛውም የሎጂስቲክስና የቴክኒካል ጉዳዮች ክፍተት በተመለከተ በየእርከኑ ባለው የምርጫ አስፈጻሚ ቦርዶች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በየጊዜው ክፍተቶች እንዲቀረፉና የምርጫ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን ይደረጋል።

በመጨረሻም፣ ሁሉም ሙስሊም በዚህ ታሪካዊ ምርጫ ላይ በነቂስ ወጥቶ እንዲሳተፍ ጥሪችንን እያቀረብን ባላ ድርሻ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር እንዲደርግልን በአላህ ስም እንጠቃለን።

ሰኔ 26 ቀን 2017፣ ሙሐረም 08 1447

የአዲስ አበባ እስልምና ጉ/ከ/ም/ቤት የ2017 ምርጫ አስፈፃሚ ቦርድ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ